የሲያትል ከተማ የመንደር አስተርዳደር

ማህበረሰብን የሚያሳትፍ የህዝብ አካዳሚ

ሲያትል እያደገች ስትሄድ፤ የወደፊት አድማሳችን ለመቀየስ አዳዲስ መሪዎች ያስፈልጉናል። ይህ ፕሮግራም የሁሉም ድምጾች የህዝብ እና የማህበረሰብ ተግባር ላይ መካፈል እና መሳተፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል።

የፕሮግራሙ ዝርዝሮች

ማህበረሰብ ለማሳተፍ የህዝብ አካዳሚ (PACE) አመራርን ማሳደግ ላይ እንዲሁም አዳዲስ መሪዎችን በርካታ ባህሎች ውስጥ ሚያሳትፍ መድረክ በመፍጠር ክህሎትን ማበልጸግ ላይ ያተኩራል። በፕሮግራሙ ውስጥ፤ ተሳታፊዎች ማህበረሰብ ለማነጽ የሚርዱ ዘዴዎችን፣ ሁሉንም የሚያካትት ተሳትፎ፣ እና በሙያ ዘርፋቸው ብቃት ያላቸውን የመንግስት ሰራተኞችን እንዴት እንደሚያገኙ ይማራሉ።

ማን ማመልከት አለበት

በቅርቡ በማህበረሰቡ ውስጥ የተሳተፉ እንዲሁም በበቂ ያልተወከሉ ማህበረሰቦችን ጨምሮ የሲያትልን አካባቢዎች የማጎልበት ሂደት ይበልጥ እውን ለማድረግ ተጨማሪ ክህሎቶችን ለማግኘት የሚፈልጉ አዳዲስ መሪዎች ናቸው።

የ PACE መርሃ-ግብር

ትምህርቶቹ የሚሰጡት ከከተማው ሰራተኞች ጋር በመሆን በርዕሱ ላይ እውቀት ባላቸው እና የቡድን ውይይቶችን የማስተባበር ልምድ ባላቸው ከማህበረሰቡ የተውጣጡ አስተባባሪዎች እና ለትርፍ በማይሰሩ ድርጅቶች ነው። የርዕሶቹ ምሳሌዎች የሚያካቱት፡-

- ግጭት ማስወገድ
- ከመንግስት ጋር መገናኘት
- ማህበረሰብ ማደራጀት
- ተሳትፎን ጠብቆ ማቆየት
- የስብሰባ ማመቻቻ
- ሕዝባዊ ንግግር
- ወደ አመራር ማድረስ
- ሁሉን የሚያካትት ዘልቆ መድረስ እና የሕዝብ ተሳትፎ

ከዚህም በተጨማሪ ተሳታፊዎች ከምመንድደሩ ቡድኖች ጋር በመሆን የማህበረሰብ ፕሮጀክቶችን ለመንደፍ፣ ለማስተባበር እና ለመተግበር በቡድን ይሰራሉ።

ትንሽ ክፍያ ይኖራል፤ ስኮላርሽፖችን ማግኘት ይቻላል።

የኢድራሻ መረጃ

ማህበረሰብ ለማሳተፍ የህዝብ አካዳሚ
የሲያትል ከተማ የመንደር አስተዳደር

ስልክ፡- **206-684-5667**
ኢሜይል፡- **Casey.Connelly@seattle.gov**
ድረ ገጽ፡- **seattle.gov/neighborhoods/peoples-academy-for-community-engagement**

Seattle Department of Neighborhoods

PEOPLE'S ACADEMY FOR COMMUNITY ENGAGEMENT